# የአጎስቲኖ ታሪክ


LIDA Italia

Billie Cejka Risnes

Loza Tadesse Mamo


5

አማርኛ am

ስሜ አጎስቲኖ ይባላል 51 ዓመቴ ነው። ስራዬ በብስክሌት ምግብ ማድረስ ነው። ሁለት ሴት ልጆች አሉኝ ግን ብዙም ኣናወራም። እኔና እናታቸው አብረን አንኖርም ምክንያቱም ተፋተናል።

ከፍቺ በኋላ የቤት ኪራይ መክፈል ስለማልችል ከእናቴ ጋር ነው የምኖረው። በዚህ ከተማ ውስጥ ኪራይ በጣም ውድ ነው።

ከጥቂት ወራት በፊት በአንድ ኩባንያ ውስጥ በጽዳት ሠራተኛነት እሠራ ነበር። የተበላሹ ነገሮችን አስተካክያለሁ፣ ሳጥኖች እሸከማለው እና ማንም በፈለገው ጊዜ እረዳ ነበር። አንድ ቀን ድርጅቱ አባረረኝ። ለምን እንደሆነ አልገባኝም።

ብዙ ሰዎች በብስክሌት ምግብ ሲያቀርቡ አየሁ። ብስክሌት መንዳት ስለምችል የአንድ ትልቅ ማጓጓዣ ድርጅት በር አንኳኳሁ። ለእያንዳንዱ ማድረስ ሦስት ዩሮ ሰጡኝ። በቀን 40€ አገኛለሁ። በጣም እድለኛ ከሆንኩ 60€ እና ደንበኞቼ የኪስ ይሰጡኛል።

የበዓል ቀን ክፍያ የለም፣ ስትታመም ክፍያ የለም፣ ባጠቃላይ ምንም አይነት መብት አላገኘሁም። ትክክል አይመስለኝም ግን ስራውን እፈልጋለሁ። አብዛኞዎቹ ሌሎች ሰራተኞች ከመላው አለም የመጡ ስደተኞች ናቸው።

ብዙ የዴሊቨሪ ሠራተኞች በየቀኑ በአደጋ ይጎዳሉ። ከዚያም አንድ የ25 ዓመት የዴሊቨሪ ሠራተኛ በመኪና ተገጭቶ ሲሞት ባለ ሥልጣናቱም እኛን ልብ ማለት ጀመሩ። ይህ ከመሆኑ በፊት መሞቱ አሳፋሪ ነው።

ከሌሎች ኩባንያዎች ከመጡ ሰዎች ጋር በመሆን ከአካባቢው ዩኒየን ጋር ስለሠራተኞች መብት ኮርስ ወሰድኩ። የሕግ ምክር በነጻ ሰጡን። የበለጠ እውቅና እና መብት ለማግኘት ታግለናል።

ከረዥም ጊዜ በኋላ ድካማችን ሁሉ ፍሬያማ ሆነ። አንድ ትልቅ የዴሊቨሪ ድርጅት ከፍተኛ ቅጣት መክፈልና ለሠራተኞች ቋሚ ሥራ መስጠት ነበረበት። በአለም ውስጥ በየትኛውም ቦታ ሲከሰት ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር። ነገሮች መሻሻል የጀመሩ ይመስላል።

# LIDA Stories

lidastories.net

## የአጎስቲኖ ታሪክ


LIDA Italia
Billie Cejka Risnes
Loza Tadesse Mamo


CC BY